# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**የከቲት 24 ቀን 2004 ዓ.ሞ.**

**መለስ የለየለት አምባገነን መሆኑን በገዛ ጉዋዶቹ ላይ አስመሰከረ፤**

**በወያኔ ቡድን ውስጥ ትርምስ መፈጠሩ ተጋለጠ፤**

**በከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ ሹም ሽር ተደረገ፤**

**ጋምቤላና ቤንሻንጉል ክልሎች በውጥረት ውስጥ መሆናቸው ተጠቆመ፤**

EthioLion.Com

በወያኔ ነባር ባለስልጣናት መሀከል ስር የሰደደ ችግር ተፈጥሮ ውስጥ ውስጡን እርስ በርስ እየታመሱ ሲሆን አንዳንዶቹም እራሳቸውን ከፓርቲው እያገለሉ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘ ው ጥቆማ አጋለጠ::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ የአንድ ሰው አምባገነንነት በፓርቲው ውስጥ ነግሶ እና ጎልቶ ከወጣ ወዲህ በተለይ የህወሀት ነባር ታጋይ የነበሩና አሁን ከፍተኛ ስልጣን ላይ ተቀመጠው ከነበሩት መሀከል አንዳንዶች በሚሰራው ስራ ደስተኛ አይደለንም በሚል ስራ እስከ ማቆም መድረሳቸውን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋልጦዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከቅርብ ግዜ ወዲህ መላ የሀገሪቱን ስልጣን ሙሉ ለሙሉ ጠቅልሎ ለብቻው ካደረገ ወዲህ አፍለኛ ካድሬ የተባሉትን የሁለት ወር የፖለቲካ እና የአመራር ሰጪነት ኮርስ እየሠጠ ከፍተኛ ስልጣን ላይ በማስቀመጡ የተነሳ የተበሳጩ የህወሀት ነባር ታጋዮች አኩርፈው ስራቸውን እስከ ማቆም መድረሳቸው ተጠቁሞዋል::

ነባር የህወሀቶቹ ታጋዮች እና የአሁኖቹ ከፍተኛ ቁንጮ ባለስልጣናት መለስ ዜናዊ ከበረከት ሰምኦን ጋር እየተሞዳሞደ በሚወስደው እርምጃ ደስተኛ ባለመሆናቸው በመበሳጨት እንዲያነጋግራቸው

እና እንዲያወያያቸው የቀድሞውን የህወሀት ሊቀመንበር ስብሀት ነጋን ቢልኩም ያልተሳካላቸው በመሆኑ አብዛኛዎቹ ስራ እስከ ማቆም መድረሳቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አስረድተዋል::

የብአዴኑ በረከት ስምኦን የወያኔን ቁልፍ ቦታ ሁሉ በእጅ አዙር ከመለስ ዜናዊ ቀጥሎ የተቆጣጠረ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮቹ መለስ ወደ ውጭ ሀገር በሚወጣበት ወቅት ጭምር ውክልና ሰጥቶት መሄዱን በተደጋጋሚ ግዜ በማረጋገጣቸው የህወሀቶቹ ሰዎች በመበሳጨት ልናዘው ሲገባ እንዴት ያዘናል በሚል እሮሮ ቢያሰሙም መለስ ዜናዊ  የሻገተ እና ያረጀ አስተሳሰብ ያነገባችሁ.....በማለት እየተሳደበ ከመመለሱም በላይ በመከላከያና በፌዴራል ፖሊስ ውስጥ የእኔ ናቸው ለሚላቸው ብቻ ቁልፍ ቁልፍ ቦታ እንዲይዙ ማድረጉን ምንጮቹ አብራርተዋል::

በአሁኑ ሰዓት ከመለስ ቀጥሎ ትልቅ የስራ ድርሻ አለው የሚባለው በረከት ስምኦን መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በአዲስ መልክ  የፓርቲውን ውስጣዊ ኃይል ማደራጀት በሚል አፍለኛ ካድሬ የሆኑትን  ወጣቶች በደህንነት እና በአስተዳደራዊ ስራ ደርበው እንዲሰሩ በሚል በየክልሉ ዋና ከተማ እየመደበ መሆኑን እና ቀጥታ ግንኙነታቸውም ከመለስ እና ከበረከት ጋር ብቻ እንደሆነም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

የካቲት 17 ቀን 2004 ዓ.ም በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ለሁለት ወር የደህንነት ስራ እና የአመራር ሰጪነት ሚና ተብሎ ኮርስ ሲሰጣቸው የነበሩት አፍለኛ ካድሬዎች የተመረቁ ሲሆን በዚሁ ምረቃ ወቅት የተጣለባችሁን አደራ በብቃት እንድትወጡና ከእንግዲህ ስልጣኑ የእናንተው ነው የሚል መልዕክት በፕላዝማ ከመለስ የተላለፈላቸው ሲሆን በዚህ ቦታ ላይ የተገኙት በሙሉ በበረከት ስምኦን አቅራቢነት በመለስ አጽዳቂነት የተሾሙ መሆኑም  ታውቆዋል::

አዲስ የተመደቡት አፍለኛ ወጣት ካድሬዎች ቢያንስ ሶስት ቋዋንቋዋ የሚያውቁ መሆን እንዳለባቸው የጠቆሙት ምንጮቹ አማርኛ እና እንግሊዝኛ መሰረታዊው ነገር ሲሆን ሌላው ከሀገር ቤት ቋዋንቋዋ አንዱን የሚያውቅ መሆን ግድ እንደሚል ገልፀው በየክልል ከተሞች የተመደቡት ካድሬዎች ቀጥታ ግንኙነታቸው ከመለስ ዜናዊ በተለይ ከበረከት ስምኦን ጋር ብቻ ሲሆን የክልል ፕሬዝዳንቶችን ጭምር እየሰለሉ ሪፖርት እንዲያደርጉ መታዘዙን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በችግር እና በውስጣዊ ትርምስ እየታመሰ ያለው የመለስ ዜናዊ መዋቅር ከበረሀ ጀምሮ ተክኖበት የመጣውን እንደ አገዳ መጦ የመጣል ስልት ተጠቅሞ ነባሮቹን እያንሳፈፈ አፍለኞቹን ስልጣን ላይ እያወጣ ሲሆን በተለይ ነባር የህወሀት ሰዎች አሁንም ድረስ  እኛ ደምተን ቆስለን መጥተን ስልጣን የሚይዘው ሌላ በሚል ዛሬም በድሮ መንገድ ጥያቄ በማቅረባቸው ያረጀና ያፈጀ አስተሳሰብ እያለ መለስ እያሳፈረ እየመለሳቸው ቢሆንም ውስጥ ውስጡን ግን ቡድኑ ከፍተኛ ችግር ውስጥ መኖሩን ምንጮቹ ጠቁመዋል::

በተለይ መለስ ዜናዊ በበላይነት የሚመራውን ጸረ ሙስና ኮሚሽንን እያብጠለጠለና እያንቋሸሸ በአደባባይ መተቸቱ ከመለስ ጋር የተፈጠረውን ክፍተት ጉልህ አድርጎ ያጋለጠ ነው ያሉት ጉዳዩን

EthioLion.Com

የሚከታተሉ ወገኖች ጥቃቅንና እዚህ ግቡ የማይባሉ ባለስልጣናትን በሙስና አሳሰርን እያሉ ማቅረባቸው የልጆች ቀልድ በሚል ስበሃት ነጋ ተናገረዋል::

ሙስናን ማጥራት ካለብን ከላይ ከቁንጮው እና ከአናት ነው ያለው ስብሀት ነጋ ለሽምግልና ተልኮ ሀሳቡ ውድቅ ስለሆነበት በመበሳጨት ብቻ ዛሬ ለሀገር አሳቢና ተቆርቋሪ በመምሰል ላይ ታች ይበል እንጂ የሀገሪቱን ሀብት ከዘረፋት ቱባ ባለስልጣናት መሀከል አንዱ ይሄው ግለሰብ በመሆኑ አድማጭም ሊኖረው አይችልም ሲሉ ጉዳዩን በአንክሮ የሚከታተሉ ወገኖች ይገልጻሉ::

ሰሞኑን አፍለኛ ባለስልጣናት ሁለት ስራ እንዲሰሩ በየክልሉ ከተመደቡ ወዲህ በተለይ የደኢህዴን እና የኦህዴድ ባለስልጣናት ላይ ያነጣጠረ የምንጠራ ዘመቻ ሊጀመር መሆኑንና ለዚሁም መንገድ መጥረጊያ ይሆን ዘንድ የአዳማ (ናዝሬት) የዞኑ ከፍተኛ ባለስልጣናትን በማንሳት መጀመሩ ታውቆዋል::

የአምስት ቢሮ ኃላፊዎች በአንድ ቀን ውስጥ ያለ ደብዳቤ ቢሮዋቸውን እያስረከቡ እንዲሰናበቱ ሲደረግ ተጠያቂ ሆነው ከተገኙ ሲያስፈልግ እንደሚጠሩ መመሪያ እየተሰጣቸው እንደተሰናበቱ ከአዳማ የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ፤የመሬት አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ፤ የኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ እና ሌሎች የሁለት ቢሮ ኃላፊዎች ድንገት ሳይታሰብ ቢሮዋቸውን አዲስ ለተሾመው ከንቲባ እያስረከቡ እንዲወጡ የተደረገ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በቅርቡ የጨፌ ኦሮሚያ ፤የደቡብ ክልል ምክር ቤት፤ የአፋር ክልል ምክር ቤቶች አስቸኳዋይ ስብሰባ እንዲያደርጉ በታዘዘው መሰረት ስብሰባቸውን ያደረጉ ሲሆን በስብሰባው ማብቂያ ላይ የተሰናበቱ ባለስልጣናት እና በምትካቸው የተሾሙት ስም በደብዳቤ እንደተገለጸላቸውም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በዚህም መሰረት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተደረገው ሹም ሽር የኦሮሚያ አስተዳደርና የህግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ መለሰ አባይነህ፤ የማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሞሲሳ ኢታና፤የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናስር ሁሴን ፤የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ብርሀኑ ንጉሴ ፤የኦሮሚያ ጽ/ቤት ሃላፊ ዘይኑ መሐመድ የተባሉት ባለስልጣናት ከቦታቸው የተነሱ ሲሆን በምትካቸው ሌሎች እንደተሾሙም ከአዳማ የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ከአዋሳ የደረሰን ዘገባ እንደሚያስረዳው ከሆነ ደግሞ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የነበሩ አራት ባለስልጣናት ሙሉ ለሙሉ ሲባረሩ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕዝዳንቱን ጨምሮ 24 ዳኞችን ሹመት በማጽደቅ ስብሰባው መጠናቀቁን ዘገባው አስረድቶዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የአድዋ ተወላጅ የሆኑ የህወሀት ባለስልጣናትን መርጦ የቅርቤ ናቸው..... በችግሬ ግዜ ሁሉ እራሳቸውን አሳልፈው ይሰጡልኛል......

EthioLion.Com

ያላቸውን ከመከላከያና ከፌዴራል ፖሊስ መሀከል እየመረጠ ቁልፍ ቁልፍ ቦታ እየሰጣቸው እንደሚገኝ የመከላከያና የፌዴራል ፖሊስ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

በህወሀት ክፍፍል ወቅት ወደ እነ ስየ አብርሀ ወግነው የነበሩና በሁዋላ አቋዋማቸውን ቀይረው ከመለስ ጋር የተለጠፉ የፌዴራል ፖሊስ ባለስልጣናት እና የመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች ብዙዎቹ የተሰናበቱ ሲሆን በአደባባይ ይቅርታ የጠየቁና የመለስን ጣኦትነት በየሄዱበት ሲመሰክሩ የከረሙት ጥቂቶቹ ግን ሰሞኑን በተደረገው የስልጣን ክፍፍል ውስጥ ትልቅ ድርሻ እየተሰጣቸው እንደሚገኝ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገልፀዋል::

በመከላከያ ውስጥ ትልልቅ ድርሻ የነበራቸው ነባር የህወሀት ጄኔራሎች በጡረታ ስም ሙሉ ለሙሉ የተሰናበቱ ሲሆን በምትካቸው ደግሞ የመለስ ቀኝ እጅ ናቸው የተባሉ ህወሀት መኮንኖች እንደተቆጣጠሩትም የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል::

ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፍቃድ  ውጭ...... ፕሬዝዳንቱ ሳያውቁ..... ፊርማቸውን ሳያሳርፉ..... በመለስ ዜናዊ ብቻ ተመርጠው ሰሞኑን ስልጣን ከተሰጣቸው የአድዋ ተወላጆች መሀከል በወያኔ ሜ/ጄኔራል የተባለው ገብራት አየለ፣ብ/ጄ/ል መሀሪ ዘውዴ፣ብ/ጄ/ል ተክለብርሀን ፣ብ/ጄ/ል ህንፃ ወ/ጊዮርጊስ ከመረጃና ደህንነት መረብ አዛዥነት እስከ የእዝ ኦፕሬሽን ሃላፊነት.....ከመከላከያ ስልጠና ዋና ኃላፊነት እስከ ኮማንዶ ጦር ዋና አዛዥነት ድረስ ለመከላከያ መኮንኖች ስልጣንና ማዕረግ የተሰጠ ሲሆን ከፌዴራል ፖሊስ ደግሞ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነርነቱ በተጨማሪ ሀሰን ሺፋ የፖሊስ ኮሌጅ የበላይ ተቆጣጣሪና አስተባባሪነት ሹመት ማግኘቱ ታውቆዋል::

በጄኔራል ማዕረግ ረዳት ኮሚሽነር በሚል በቅርቡ ማዕረግ ከተሰጣቸው የፌዴራል ፖሊስ መኮንኖች መሀከል የአድዋ ተወላጅና የመለስ ታማኝ የተባሉት ጄኔራል ዘይድ ገብራይ -የአስተዳደር ክፍል ኃላፊ ፣ጄኔራል አለምጸሀይ ካሳ በመላ ሀገሪቱ የተወርዋሪ እና የጥበቃ ሃላፊ፣ ኮማንደር ዘላለም ደስታ የወርቅነህ ገበየሁ  ዋና ጸሀፊ እና ልዩ ተቆጣጣሪ፣ኮማንደር አበበ ዘሚካኤል የህዝብ ግንኙት ኃላፊ እና  ሌሎችም የህወሀት ሰዎች መሾማቸው ተረጋግጦዋል::

ከመከላከያና ከፌዴራል ፖሊስ ተቋዋም በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ውስጥ የአድዋ ተወላጅ የሆኑት ሰዎች እየተመረጡ እና የዘር ሀረጋቸው ብቻ እየተመዘዘ ከፍተኛ ስልጣን እየተሰጣቸው መሆኑን የቤተክህነት ምንጮች ጠቁመው መለስ ዜናዊ በቅርቡ የጀመረው መንደርተኝነት አደረጃጀትን በስፋት እየሰራበትና በሁሉም ተቋዋም ውስጥ እያስፋፋ መሆኑን ያረጋገጠ ነው ሲሉ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በሌላ ዜና  ከኢትዮጵያ ህዝብ እውቅና ውጭ በሱማሊያ ገብቶ እየዳከረና እያለቀ ያለው የወያኔ ጦር በመላ ሀገሪቱ አዲስ ቁጥጥር በሚል ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተበተነ እንደሚገኝ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

ሰሞኑን በቤንሻንጉል እና በጋምቤላ ክልሎች ውስጥ የተፈጠረው ነገር ባይታወቅም ሁለት ከባድ መሳሪያ የታጠቁ ክፍለ ጦሮች ወደ ክልሎቹ የገቡ ሲሆን በበላይነት ባህርዳር የሚገኘው እዝ እንደሚመራቸውም ምንጮቹ አጋልጠዋል::



EthioLion.Com

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከዚህ ቀደም ቤህነግ (የቤንሻንጉል ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር) የተባለ ወያኔን በትጥቅ የሚፋለም ድርጅት እንደነበረ በስፋት ሲዘገብ የቆየ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከዚሁ ድርጅት ጋር ይሁን ከሌላ በትክክል ባልታወቀ ሁኔታ ከፍተኛ ስጋት ላይ ስለወደቁ 44ኛ ዳሎል ክፍለ ጦር የተሰኘ በከባድ መሳሪያ ታገዘ ጦር ወደ ስፍራው ማቅናቱን ምንጮቹ ገልጸዋል።

ከዚህ ክፍለ ጦር በተጨማሪ 43ኛ ክፍለ ጦር ደግሞ ወያኔ የአኬልዳማ ምድር ያደረጋት ወደ ጋምቤላ የተላከ ሲሆን በዚህም በተመሳሳይ ለወያኔ ከፍተኛ የስጋት አቅጣጫ እንደሆነበትም ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል።

በተለይ ይሄው 43ኛ ክፍለ ጦር የተሰኘው የጦር ከፍል ውስጥ ያሉ መኮንኖች እና የሰራዊቱ አዛዦች የታዘዙትን ሁሉ እንዲፈጽሙና እንዳያንገራግሩ የማዕረግ እድገት እና የተለያዩ መለማመጫ ሽልማቶችን የሰጡዋቸው መሆኑም ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

በጋምቤላ ክልል ውስጥ ከዚህ ቀደም የወያኔ ጦር በመትረየስ ቤት ለቤት እየዞረ የአኙዋክ ብሔር ተወላጆችን የጨፈጨፋቸው ሲሆን ከዚያ ግዜ በሁዋላ በአካባቢው ችግሩ ተባብሶ በመቀጠሉ በአሁኑ ወቅትም ክልሉ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደሚገኝ ታውቆዋል።

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ደግሞ በግዳጅ ሰፈራ በሚል ህዝቡን እትብቱ ከተቀበረበት ቀዬ እያፈናቀለ መውሰድ በመጀመሩ የተነሳ በተፈጠረ ግጭት እጅግ ቁጥራቸው የበዛ የኑዌር እና የአኙዋክ ብሄር ተወላጆች በወያኔ ሰራዊት እየተደበደቡ ከመሆኑም በላይ እስከ አሁን ድረስ ከ20 ሰዎች በላይ እንደተገደሉም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል።

የሰፈራ ፕሮግራሙን በተቃወሙት ዜጎች እና በወያኔ መሀከል በተፈጠረ ግጭት እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ለስደት እየተዳረጉ ባለበት ወቅት በክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ በተደረገ ግምገማ እና በተወሰደው የማባረር ዘመቻን ተከትሎ ከፍተኛ ውጥረት በመንገሱ ቀድሞ ከነበረው ጦር በተጨማሪ 43ኛ የተሰኘው ክፍለ ጦር በከባድ መሳሪያ ታግዞ ወደ ስፍራው ማቅናቱ ሁኔታው እጅግ አሳሳቢ ሲሆን እንደቻለም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

የስልጣን እድሜውን በመሳሪያ ኃይል ለማራዘም ላይ ታች እያለ የሚገኘው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን ከቅርብ ግዜ ወዲህ በህዝቡ ላይ እያደረሰ ያለውን አፈና አገዛዝ አስፋፍቶ መቀጠሉ እጅግ አሳዛኝ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይ በጋምቤላ ክልል ውስጥ እየፈጸመ ያለው ዘግናኝ ግፍ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመሄዱ ህዝቡ ሳይወድ በግድ ወደ ስደት ሊገባ እንደቻለና የተቀሩትም በቡድን በቡድን በመሆን የትጥቅ ትግል መጀመራቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ ግዳጅ ላይ ተሰማርተው ከሚገኙት የጦር ክፍሎች ውጭ በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ተበትነው የሚገኙት የጦር ክፍሎች ውስጥም ያሉ መኮንኖች እና የበታች ሹሞች በአዲስ መልክ የውጊያ ልምምድ እያደረጉ ሲሆን ወያኔ በአሁኑ ግዜ ይህን ማድረጉ በሀገሪቱ ምን ተከስቶ ይሆን ሲሉም መኮንኖቹ እየጠየቁ ይገኛሉ።

EthioLion.Com

EthioLion.Com